ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

እሮብ ግንቦት 20 2000 ዓ.ም

**ኩማ ደመቅሳ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆነ። የመከላከያ ሚነስትርነቱን ቦታ ለመውሰድ ቋምጠው የነበሩት ሕላዊ ዮሴፍ በኤታ ማጆር ሹሙ በጄነራል ሳሞራ ዩኑስ ሲያምርህ ይቅር ተባሉ።**

በቀድሞ መንግስት ጦር የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት አባል የነበረው ታየ ተክለማርያም ባሁኑ መጠሪያው ኩማ ደመቅሳ ከመከላከያ ሚንስትርነት ወደ አዲስ አበባ ከንቲባነት ተሹሞአል።የቀድሞው ወታደርና የሻእቢያ ምርኮኛ የነበረው ኩማ ደመቅሳ ኦህዴድ በተባለውን የህወሃት ጉዳይ አስፈጻሚ ድርጅት ጋር ተቀላቅሎ ሃላፊነትን ሳይጨብጥ በትግሉ ጊዜ በህወሃት ነጻ መሬት ህጻናትን ፊደል በማስተማር ያገለገል እንደነበር የሚያውቁት ይናገራሉ።
ኦህዴድን ህወሃት ሲመሰርት ኩማ የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆኖ ያገለገለ ሲሆን፡ በሽግግሩ ወቅት የሃገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስትር፣ከዛም በመቀጠል የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንትነትን ይዞ እንደነበር የሚታወስ ነው። ሆኖም በህወሃት መሃከል መከፋፈል ሲፈጠር በሙስናና ለአንጃው ወግነሃል በመባሉ ከሃላፊነቱ ተነስቶ እንደነበር ይታወሳል።

የስኳር ህመምተኛ የሆነው ኩማ፣ በወቅቱ በአይኑ ላይ ከባድ ህመም ደርሶበት የውጭ ሃገር ህክምና ከመከልከሉ ባሻገር ወደጎን ተጥሎ እንደነበር ሳገዛዙ ቅርበት ካላቸው መንጮች ለመረዳት ችለናል።

በምርጫ 1997 ወቅት በኢሉባቦር ዞን ጎሬ አካባቢ ኦህዲድን ወክሎ በብቸኝነት ተወዳድሮ ብቻውን አሸንፏል። ኩማ ከትምህርት ጋር የተጣላ ሰው ቢሆንም እንደነተፈራ ዋልዋ በ15000 ዶላር በመንግስት ወጭ የተገዛ የሃሰት ዲግሪ ባለቤት መሆኑ ታውቋል። እንደ ተንታኞች አስተያየት ግለሰቡ ካለው ደካማ ችሎታና የትምህርት አቅም አዲስ አበባን የሚያክል ትልቅ ከተማ መምራት ቀርቶ የአንድ መንደር ጎበዝ አለቅነት ይበዛበታል።

በተያያዘ ዘገባ በምርጫ 97 ወቅት በዝረራ የተሸነፈው ሕላዌ ዮሴፍ፡(ቦጌ) ከአዲስ አበባ የብአዴን ዋና ጸሃፊነት ወደ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ድርጅት ስራ አስኪያጅነት ሊሸጋገር መሆኑ ተሰማ።

አቶ ኩማ የለቀቀውንን የመከላከያ ምኒስትርነት ቦታ በይፋ መፈለጉን ያስታወቀው ህላዌ ጥያቄው በኢታማጆር ሹሙ ጀነራል ሳሞራ ይኑስ እንቢተኝነት ሳይሳካለት መቅረቱን ለጉዳዮ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልጸውልናል። አቶ ህላዊ በትምህርት በኩል 11ኛ ክፍልን በቅጡ ካለማጠናቀቁም ባሻገር ወደ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ለመግባት የሚጠይቀውን አነስተኛ መመዘኛ ማሟላት ያልቻለ መሁኑን ለማወቅ ተችሎአል። በእዚህ ደካማ እውቀቱ የመከላከያ ሚኒስቴርነት ቦታ መመኘቱ ብዙዎችን ያነጋገረ ጉዳይ ቢሆንም፣ ዋናው የአቶ ህላዊ አላማ ስልጣን ሳይሆን በመከለከያ ሚንስቴር ውስጥ በሚካሄደው አይን ያወጣ ዘረፋ ተካፋይ ለመሆን በማሰብ የተደረገ ነው ይባላል። የመከላከያ ሚንስቴርነቱን ቦታ ማን ይወስደዋል የሚለው ጥያቄ በወያኔ ኢህአዴግ ውስጥ አነጋገሪ ሆኗል።